# የወ/ሪት ብርቱካን ሚዴቅሳ በድጋሚ መታሰር
# ለኢትዮጵያውያን የተበረከተ የገና ስጦታ መሆኑ ይኾን?

የ"አንድነት" ለዴሞክራሲ እና ለፍትሕ ፓርቲ ሊቀ መንበር ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ታኅሳስ አንድ ቀን 2001 ዓ.ም የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽነር ዘንድ ተጠርታ "ሃገረ ስዊድን አንድነት በጠራው ስብስባ ላይ ከእስር የተፈታነው ይቅርታ ጠይቀን አይደለም ብለሻል" ተብላ መጠየቋን፤ ታህሳስ 15 ቀን 2001 ዓ.ም ላይ ድግሞ "ሰዊድን የተናገርሽውን በሶስት ቀናት ውስጥ ካላስተባበልሽ ተመልሰሽ ትታሰሪያለሽ" መባሏን ሰማን፡፡ ይህን ማሳሰብያ ተከትሎ ቅዳሜ ታህሳስ 18 በወጡ ሁለት ጋዜጦች "ቃሌ" ይህ ነው ብላ መልሷን ይፋ ያደረገች ቢሆንም "አላስተባበልሽም" በሚል መታሰሯን ሰኞ ዕለት ማምሻውን የፍትህ ሚኒስቴር በሰጠው መግለጫ ተነገረን፤ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ቃል አቀባይም ድርጊቱ የፖለቲካ ሳይሆን "የህግና የቴክኒክ" ጉዳይ ነው ብሎናል፡፡

ወ/ሪት ብርቱካንም መንግስትም የሰጡትን ቃልና መግለጫ አዳምጠናል፤ ከሁሉም በላይ ጮኾ የተናገረው ግን ድርጊቱ ነው፡፡ መታሰሯ! "አላስተባበልሽም" ተብላ የእድሜ ልክ እስራቷን ለመቀበል በድጋሚ ቃሊቲ መግባቷ!

ወ/ሪት ብርቱካን የታሰረችው በፈረንጆቹና በእኛው ገና መሃከል ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ ጊዜው የምዕራቡ ዓለም ገናን የሚያከብርበት፤ አዲሱን የፈረንጆች ዓመት የሚቀበልበት የዕረፍትና የፌሽታ ወቅት በመኾኑ በዚሁ ወቅት የሚከሠት ሁኔታ ብዙ ትኩረት አያገኝም፡፡ በሕግ የተሰጠን ይቅርታ በሕጋዊ መንገድ ለማንሳት ከተፈለገ የሚመለከተው ዜጋ አስቦበት መልስ ይሰጥ ዘንድ የኻያ ቀን ገደብ እንደሚሰጠው የይቅርታ ሕጉ ቢደነግግም የኢህአዴግ መሪዎች ይኸው "የሕግና የቴክኒክ" ጉዳይ እስኪሚላ ድረስ አለመታገሳቸው፤ አይደለምና እርምጃው የጊዜ መረጣው ራሱ "የሕግና የቴክኒክ" ጉዳይ እንዳልሆነ ያመለክታል፡፡

ወ/ሪት ብርቱካን የታሰረችበት ጊዜ ከሁለት አመት በፊት የሃገር መከላከያ ስራዊታችን የሶማልያ እስላማዊ ፍርድ ቤቶች ሕብረትን ለመምታት መሰማራቱ ይፋ ከተደረገበት ወቅት ጋር የሚያመሳስለው ነገር ይታይበታል፤ ያኔም ወታደራዊ ጣልቃ ገብነቱን ገቢራዊ ለማድረግ የተመረጠው ወቅት ይህ በፈረንጆቹ ገና እና አዲስ ዓመት አካባቢ ያለው "አሳቻ ወይም ሰዋራ ወቅት" ነው፡፡ የወቅት መረጣው የጣልቃ ገብነቱን ኮቴ ተከትሎ ሊመጣ ይችል የነበረውን የዓለም አቀፉን ማኅበረሰብ ሒስና ውግዘት ለአጭር ጊዜም ቢሆን አዘግይቶት ነበር፤ ከቶ እንዳላስቀረው ግን ባለፉት ሁለት ዓመታት ሂዩማን ራይትስ ዎች የተባለው የስብአዊ መብት ተሟጋች ያወጣቸው ዘገባዎች ያመለክታሉ፤ የወ/ሪት ብርቱካንን ዳግመኛ መታሰርን ገቢራዊ ለማድረግ ይህ ወቅት መመረጡም አሰቀያሚውን ድርጊት ለትንሽ ጊዜ ይሰውረው እንደኾነ እንጂ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ትልቅ መነጋገርያ ጉዳይ ከመኾን አያስቀረውም፤ መሰረታዊ የፖሊሲ ስህተትን በስልታዊ ብልጣብልጥነት ለመደባበቅ አይቻልምና፡፡

ምርጫ 97ን ተከትሎ በተፈጠረው ውዝግብ በቁጥጥር ስር የዋሉ የቀድሞው የቅንጅት አመራሮችን፣ የሲቪል ማኅበረሰብ አባላትን እና ጋዜጠኞችን ጉዳይ ለመዳኘት በቃሊቲው ከርቸሌ አጠገብ የተሰየመው ችሎት ክስና ማስረጃ ቢያዳምጥም በስተመጨረሻው ነገሩ የፖለቲካ እንጂ የሕግ እንዳልሆነ ኢህአዴግም በመገንዘቡ ነበር ሽማግሌዎች እንዲገቡበት የፈቀደው፡፡ ኢህአዴግ ባይፈቅድ ኖሮ እነዚያ ሽማግሌዎች

እስረኞቹን ሰብስቦ ማናገር ይቅር እና ወደ ቅጽር ግቢው ውስጥ መግባት እንኳ አይችሉም ነበር፡፡

ጥሪቱ ዳር ደርሶ ወ/ት ብርቱካን እና በልደረቦቿ ሲፈቱ እርምጃው የኢትዮጵያን የሁለት ሺኛው አመት ማብቂያ፣የሦስተኛው ሺሕ ዓመት መሸጋገርያ ላይ የተደገሰው የሚሊንየም በአል ላይ ትልቅ ስፍራ እንደተሰጠው እና "አዲሱ ሚሊንየም የዕርቅ፣ የብሔራዊ መግባባት እና የኢትዮጵያ ሕዳሴ ዘመን ይኾናል" ሲባል እንደነበርም ይታወቃል፡፡ ያ ሽምግልና ያልነበረና ያልተፈለገ ይመስል፤ ወ/ት ብርቱካን ሌላ ፓርቲ ይዛ ብቅ ስትል እና ምርጫ - 2002 እየተቃረበ ሲመጣ ስዊድን አገር እንደዚህ ብለሽ ነበርና ካላስተባበልሽ ብሎ ያልተከላከለችበትንና፣ ይግባኝ የማለት እድል የተነፈገችበትን፣ ፋይል ቀስቅሶ "እድሜ ልክሽን ታሰሪ" ማለት እነዚያ አንቀላፍተው የነበሩት፤ ምርጫ 97ን ተከትሎ የተቀስቀሱትን አቤቱታዎችና ፋይሎችን በሙሉ እንደ አዲስ መቀስቀሱ የማይቀር ነው፡፡

የተወሰኑ ፓርቲዎችና ፖለቲከኞች "የምክክር መድረክ" መሰረቱ ሲባል የኢህአዴግ መንግስት የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዴሞክራስያዊ ንቅናቂ (ኦፌዴን) ዋና ጸሐፊን አቶ በቀለ ጅራታን ጨምሮ በርካታ የኦፌዴን እና የኦሮሞ ሕዝብ ኮንግሬስ (ኦሕኮ) አባላትን በማሰር መድረኩን የመሰረቱትን ፓርቲዎች የማሽመድመዱን ዘመቻ ጀመረ፡፡ "አንድነት" ለዴሞክራሲና ለፍትህ ህጋዊ እውቅና ካገኘ ወዲህ ለመጀመርያ ጊዜ በአዲስ አበባ የጠራውን የኅዳር 27 ቀን ሕዝባዊ ስብሰባ ተከትሎ ወ/ሪት ብርቱካን በስዊድኑ ጉዳይ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር ቢሮ ዘንድ ተጠራች፤ ከዚያ በኋላም ብዙ ሳትቆይ ወደ እስር ቤት ገብታለች፡፡

ኢህአዴግ ምርጫ - 2002ን እያሰበ ከወዲሁ እየወሰዳቸው ያሉት የ"በእንጭጩ" እርምጃዎች የምርጫ 97ን ፋይሎች በመክፈት ሁለቱንም ምርጫዎች በፈጣን ባቡር እያስተሳሰረ ያለ ይመስላል፡፡ "በእንጭጩ" የሚለው አባባል "እውን አደጋ ባያመጣም አደጋ ያመጣል ተብሎ ከተገመተ አስቀድሞ መምታት ተገቢ ነው" ከሚለው የቡሽ - ቼኒ የ"አስቀድሞ መምታት አቋም (እምነት)" (Pre-emptive strike doctrine) ጋራ የሚመሳሰል አገርኛ ዘይቤ ነው፡፡ ይህንን ዘይቤ የሃገር መከላከያ ሚኒስቴር ቢጠቀምበት ላያስገርም ይችላል፤ ይህን ያለው የፍትህ ሚኒስቴር መሆኑን ለሰማ ግን ከማስገረሙም ባሻገር በሁለቱ ሚኒስቴሮች መካከል ያለው ድንበር ምን ያክል እንደደበዘዘ የሚያመለክት ነው፡፡

ፍትህ ሚኒስቴር ይህንን ፅንሰ-ሓሳብ ገቢራዊ ማድረግ የጀመረው በኦፌዴንና በኦህኮ ሲሆን አሁን በመጨረሻ ደግሞ ወደ "አንድነት" ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ተሸጋግሯል፡፡ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ በኢትዮጵያ "በሰላማዊ ትግል ለውጥ ለማምጣት ይቻላል" ብላ እና በዚሁ ጉዳይ ከገዛ ባለንጀሮቿ ሳይቀር ተለያይታ በአዲስ መልክ በመደራጀት ሰላማዊ ትግልን አጥብቃ የያዘች ፖለቲከኛ ናት፤ ለህግ የበላይነት በጽናት መቆም ማለት ምን እንደኾነ በተግባር ያስመሰከረች የህግ ባለሙያ ናት፤ በሃገራችን የመጀመርያ ወጣት ሴት የፓርቲ መሪ ናት፤ የልጅ እናትም ነች፡፡ የእርሷን ማንነት የሚገልጹት እነዚህ ግዙፍ እውነታዎች መሆናቸው እየታወቀ ተዘጋ ሲባልለት የቆየውን የምርጫ 97 አታካራ ቀስቅሶ አሁን እርሷን መልሶ ማሰር ኢህአዴግ 97ን እያሰበ 2002ም እንደዚያው እንዳይኾንበት ከአሁኑ ጀምሮ የ"በእንጩጩ" ስትራተጂውን ተግባራዊ እያደረገ መኾኑን ያመለክታል፡፡

እነዚህ እርምጃዎቹ የሚያመለክቱት የኢህአዴግ ጥንካሬን ሳይሆን ፓርቲው ለሰላማዊ ትግልና ለሰላማዊ ታጋዮች ያለውን ፍርሃት ነው፡፡ አሁን ብቅ ብቅ ማለት የጀመረው የፓርቲዎች የመጠናከርና የመተባበር አጀንዳ ፋታ ተሰጥቶት አንዱ ብድግ

ካለ እንደ 98ቱ ሀምቪዎችንና ኮማንዶዎችን አሰማርቶ ልምታ ቢባል እንኳን ውጤቱ እንደ ያኔው ላይሆን ስለሚችል ከዚያ ይልቅ የተሻለ ሆኖ የተገኘው፣ ሰበብ እየፈጠሩ የትብብር ሰንሰለቱን ሊያቆላልፉ ይችላሉ የተባሉትን ቁልፍ ሰዎች እየለዩ አንድ በአንድ መምታት ነው።

ገዢው ፓርቲ በዚህኛው ስትራተጂ ሊያሳካ የፈለገው ግብ ተቃዋሚዎች ጨርሰው እንዲጠፉ ከማድረግ ይልቅ እያንዳንዱ ፓርቲ በውስጣዊ ጉዳዩ የድርጅቱን ህልውና በማስቀጠል ብቻ ተጠምዶ ሌላውን ጉዳይ ለመስራትና ለመመልከት እንዳይችል ማድረግ ነው። በዚህ አካሄዱ ፓርቲዎቹ ብድግ ብለው ወደፊት መራመድ ሲጀምሩ አንድ የተመረጠ ምት ይሰነዝርና በዚሁ ምት ምክንያት የተበተነውን ቋጠሮ ለማሰር ተመልሰው ቁጭ እንዲሉ ያደርጋቸዋል። ይህንን ካሳካም ፓርቲዎቹ እንደደከሙና እንደተበታተኑ ምርጫ - 2002 ይደርሳል።

ኢህአዴግ ወትሮውም እንደሚለው "ፓርላማውን ማምቀሪያ ጨው" እንዲሆኑለት ብሎ ለተወሰኑት እና በስም ለሚታወቁት የፓርቲ መሪዎች የምርጫ ወረዳቸውን ያለተወዳዳሪ ሊተውላቸው ይችላል፤ ምርጫ - 2002 ላይ ጠንካራ ፉክክር ማየት እንደማይፈልግ ግን ሚያዝያ 2000 ላይ በተደረገው ምርጫ በግልፅ አሳይቷል። ተፎካካሪ ፓርቲዎች ማምቀሪያ ጨው ከመሆን ሊተርፉ እና የኢህአዴግን የ"በእንጭጩ" ስትራተጂ ሠብሮ ለማለፍ የሚችሉት አጠቃላይ የአስተሳሰብ እምርታ (paradigm shift) ካመጡ ብቻ ነው። ጊዜው ሳይረፍድ፣ ውስጣቸውን ለአዲስ አስተሳሰብና አዲስ አካሄድ ክፍት በማድረግ ስለተናጠል ሳይሆን ስለ ጋራ ህልውና ማሰብ ከቻሉ የኢህአዴግን ስትራተጂ ጥሶ ማለፍ ይቻላቸዋል። በወ/ሪት ብርቱካን ሚዲቅሳ፣ በአቶ በቀለ ጅራታ እና በሌሎችም ወገኖቻችን እየደረሰ ላለው እስርና እንግልት ሊሰጥ የሚገባው ዘለቄታ ያለው መልስም ይህንን ማሳካት ነው።

ስየ አብራሃ
ታኅሳስ 29 ቀን 2001 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

**************

*ይህ ጽሑፍ ጥር 2 ቀን 2001 ዓ.ም በወጣው የአዲስ ነገር ጋዜጣ እትምም ወጥቷል
*የእኔን አድራሻ ለሚሹ፦ seabrag@gmail.com